በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 213758

ቀን ግንቦት 23 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፊይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. ወ/ት ሰንሰለት ወንድይራድ ጠበቃ አገኘሁ መኮንን ቀረቡ

2ኛ. አቶ ምርጥዘር ወንድይራድ -- ቀረቡ

3ኛ. አቶ ሰውነት ወንድይራድ - ወኪል 2ኛ አመልካች ቀረቡ

4ኛ. አቶ በተለይ ወንድይራድ -- ጠበቃ አለማየሁ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ አዳነ ተ/ሃይማኖት -ጠበቃ ሄየለ ጫላ ከ1ኛ አመልካች ጋር ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ አልማዝ ተ/ሃይማኖት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ በኮ.መ.ቁ 116047 በ21/9/12ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 257494 በ10/10/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ1/13/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ 1ኛ አመልካች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች እና በ4ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ አያቴ ሲሆኑ በአዲስ አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ 008፤ 008/09 እና 029 ቤት የነበረ ሲሆን አያቴ ከሞቱ በኋላ የውርስ ሀብት በሆኑት ቤቶች ውስጥ እስከ 21/4/06ዓ.ም ድረስ የቆየሁ ሲሆን ከዚህ ግዜ በኋላ ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(ስር ተከሳሾች) ለብቻቸው በመያዝ ክስ እስከቀረበበት ግዜ ድረስ ብር 258,000.00 የውርስ ገንዘብ ሰብስበዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ የ1ኛ አመልካች ድርሻ ብር 12,900.00 እና ወደፊት በቤቱ ላይ ድርሻዬን እስከማገኝ ድረስ የሚኖረው ክፍያ ታስቦ እንዲከፈለኝ፤ ሟች አያታችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆኑ አራት ልጆች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የ1ኛ አመልካች አባት አቶ ወንድይራድ አለማየሁ አምስት ልጆች ያላቸው በመሆኑ የአባቴን ድርሻ 1/5ኛ ከቤ.ቁ 008፤ 008/09 እና 029 ድርሻ እንዲያካፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ የተደረገ ሲሆን በአማራጭ ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች ክስ ባቀረቡበት የቤ.ቁ 008/09 እና 029 ውስጥ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ከመሞታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ቤቱ ውስጥ ኖረው አያውቁም፡፡ የሚኖሩት በመንግስት በተወረሰ የቤ.ቁ 007 በሆነ የቀበሌ ቤት ውስጥ ከእናታቸው ጋር ነው፡፡ የቤ.ቁ 029 ከ1968ዓ.ም ጀምሮ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ሲሆን የቤ.ቁ 008/09 ደግሞ የኑዛዜ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ከ1997ዓ.ም ጀምሮ በውርስ ያገኙት የግላቸው ነው በማለት ተከራክረው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች የሟች የደረጃ ወራሽ ናቸው፤ 4ኛ አመልካችም ከአውራሽ ጋር በአንድ ቤት ውስጥ እኖር ስለነበር በሰሩት አንድ ክፍል ቤትና የውርስ ሀብት በሆነው ይዞታ ላይ በራሴ ወጪ ጨምሬ በሰራሁት አንድ ክፍል ቤት በድምሩ 2 ክፍል ቤት ይዤ እያከራየሁ እየተጠቀምኩ ነው፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች የጠየቁት በአግባቡ በመሆኑ የውርስ ሀብቱን እንደድርሻችን እንካፈል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የደረጃ ወራሾች ስለሆንን የምንኖረው አረብ አገር ስለነበር ስንመጣ 1ኛ አመልካች እና 4ኛ አመልካች እንዲሁም ተጠሪዎች ክርክር ላይ መሆናቸውን ስላረጋገጥን የአባታችንን ድርሻ ልናገኝ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃገብተን እንድንከራከር በማለት በጠየቁት መሰረት ወደ ክርክሩ ገብተዋል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ከሰማ እና የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የውርስ ሀብት ነው ወይንስ የ1ኛ ተጠሪ የግሉ? ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(የስር ተከሳሾች) የያዙት የውርስ ሀብት የቱ ነው? ምን ያህል የኪራይ ብር ሰብስበዋል? ሊከፍሉ ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች ከያዘ፤ የ1ኛ አመልካች እና የተጠሪዎችን ምስክሮች ከሰማ፤ ማስረጃ ተጣርቶ እንዲላክ ለየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት እና ለየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ምላሽ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከቀረበለት በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጭምር ጉዳዩን መርምሮ የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት ሟች በህይወት እያሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ በሰጧቸው ይዞታ ላይ ቤት በራሳቸው ወጪ ሰርተው እንደሚኖሩ የ1ኛ እና የተጠሪዎች(ስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች) ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ላይም የቤ.ቁ 029ን ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተውት የነበረና በራሱ ወጪም ቤቶችን ሰርቶ እንደሚኖር ገልጸዋል፡፡ ይህ ኑዛዜም በስጦታ ተሰጥቶ ቤቶች ሰርቶ መኖሩን እውቅና የሰጠበት እንጂ እንደአዲስ በኑዛዜው ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው መብት የለም፡፡

1ኛ ተጠሪ በቤ.ቁ 029 ላይ ከ1968ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር የሚከፍሉበት በስማቸው እንደሆነ ከቀረቡት የተለያዩ የግብር ደረሰኞች ተረጋግጧል፡፡ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ከመሞታቸው በፊት በ1992ዓ.ም የወረዳ 15 ቀበሌ 19 አስተዳደር ጽ/ቤት የቤ.ቁ 029 1ኛ ተጠሪ በራሳቸው ከአ/ቁ 47/67 በፊት የሰሩ መሆኑን በምስክር ማረጋገጣቸውን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ሟች በኑዛዜያቸው ይህን እውቅና የሰጡ ከመሆኑ ውጪ እንደ አዲስ መብት የሚሰጥ ስላልሆነ የኑዛዜው መሻሻልና የሟች ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ መስጠቱ 1ኛ ተጠሪ ሟች በህይወት እያሉ ተፈቅዶለት የሰራቸው እና ባለመብት የሆነባቸውን ቤቶች ወደ ውርስ ሀብት በማስገባት እንዲያካፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ የቤ.ቁ 029 ሟች በህይወት እያሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ተሰጥተው የሰሯቸው ቤቶች መሆናቸው ከሟች ኑዛዜ ቃል፤ ከቀረቡት ምስክሮች እንዲሁም ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ከተሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ቤቱ የውርስ ሀብት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪዎች እና 4ኛ አመልካች(ስር ተከሳሾች) የያዙት የውርስ ሀብት የቱ ነው የሚለውን በተመለከተ የቤ.ቁ 029 የ1ኛ ተጠሪ የግሉ ቤት ነው የተባለ በመሆኑ የያዘው የውርስ ሀብት የለም፡፡ 2ኛ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) የቤ.ቁ 008 እና 008/009 የሚባለው በውል የሚጠቀሙበት 008 በሚል መሆኑ የተረጋገጠውን ቤት በኑዛዜ የያዙ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ሲሆን ይህ ኑዛዜም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ ኑዛዜው ተስተካክሎ 1ኛ አመልካችም አባታቸውን በመወከል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የወሰነ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ የያዙት የቤ.ቁ 008 የውርስ ሀብት ነው፡፡ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) የቤ.ቁ 008 ጋር የተያያዘ ሁለት ክፍል ቤት የያዙ መሆኑን፤ የውርስ ሀብት ተደርጎ መከፋፈል እንዳለባቸው በመልሳቸው አምነው የገለጹ ስለሆነ የውርስ ሀብት ነው፡፡

ምን ያህል የኪራይ ገንዘብ ሰብስበዋል የሚለውን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ የሰበሰቡት የኪራይ ገንዘብ የግል ንብረታቸው/ይዞታቸው በሆነው ቤት ላይ ስለሆነ የኪራይ ገንዘቡ የውርስ ሀብት አይደለም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ከቤ.ቁ 008 ላይ ሁለት ቤት አከራይተው ገንዘብ የሰበሰቡ መሆኑን የተረጋገጠ ሲሆን የኪራይ መጠኑን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ከገቢዎች በተረጋገጠው መረጃ መሰረት የወሰደ ሲሆን ይህም በወር ብር 1500.00 የሚሰበሰቡ ሲሆን ከ2006ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ግዜ የ2 አመት ከ6 ወር ብር 45,000.00 መሰብሰባቸው በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) ከቤ.ቁ 008 ላይ ብር 1500.00 በወር

ያከራዩ መሆኑን ከገቢዎች በተገኘው መሰረጃ መሰረት ተወስዶ የሚያከራየውም ከ2008ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ምስክሮች ስላረጋገጡ ከመስከረም 2008ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 2000ዓ.ም ድረስ የ10 ወር ብር 15,000.00 የውርስ ሀብት መሰብሰባቸው በማስረጃ በመረጋገጡ ይህን የሰበሰቡትን የውርስ ሀብት የኪራይ ገንዘብ ለወራሾች እንደደርሻቸው የሚያከፋፍሉ ይሆናል፡፡

የውርስ ሀብት ክፍፍሉን በተመለከተ የሟች የውርስ ሀብት በ2ኛ ተጠሪ እና በ4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ) የተያዙት የቤ.ቁ 008 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች አራት መሆናቸው አልተካደም፡፡ ሟች በኑዛዜያቸው ላይ ለወንድሜ ልጅ ሸዋረግ ወርቁ በማለት ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ፤ ይህም ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የኑዛዜው ተጠቃሚዎች  በኑዛዜው የተነቀለው የ1ኛ አመልካች አባት እኩል ተካፋይ እንደሚሆኑ ስለገለጸ የውርስ ሀብቱ እኩል ተካፋይ የምትሆን ይሆናል፡፡ ስለሆነም የውርስ ሀብት ተካፋዮች አምስት ናቸው፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ የያዘው የቤ.ቁ 029 ከ11 ክፍል በላይ ስለሆነ ይህም በውርስ ከሚደርሰው ድርሻ በላይ ስለሆነ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1062(2) እና 1063(1) ከደነገጉት አንጻር የያዘውን ለመመለስ የማይገደድና ከውርስ ሀብቱ ላይም ድርሻውን እንደወሰደ የሚቆጠር በመሆኑ የውርስ ሀብት ተብሎ የተጠቀሰውን ንብረት ወይም ቤት የቀሩት የሟች ሶስት ልጆችና የኑዛዜ ወራሽ የሆኑት ግለሰብ እኩል የሚከፋፈሉ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የቤ.ቁ 008 ላይ ያሉ ቤቶችን 2ኛ ተጠሪ 1/4ኛ፤ የኑዛዜ ወራሽ የሆኑት ሸዋረጋ ወርቁ 1/4ኛ፤ አቶ ሰለሞን አለማየሁ 1/4ኛ፤ ቀሪ የሟች ወንድይራድ አለማየሁ ድርሻ የሆነውን 1/4ኛ ድርሻ ተተኪ ወራሾች የሆኑት 1ኛ አመልካች፤ 4ኛ አመልካች(ስር 3ኛ ተከሳሽ)፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች(ስር ጣልቃገቦች) እያንዳንዳቸው የ1/4ኛውን ድርሻ 1/5ኛ የሚደርሳቸው ይሆናል፡፡ ስለዚህ የሟች የውርስ ሀብት የሆነውን የቤ.ቁ 008 ከላይ የተጠቀሱት ወራሾች ከተቻለ በአይነት፤ ካልሆነም በስምምነት፤ ስምምነት ከሌለም በሐራጅ ተሸጦ ሊከፋፈሉ ይገባል፡፡

ከውርስ ሀብት የተሰበሰበውን የቤት ኪራይ በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ ከሰበሰቡት ብር 45,000.00 ውስጥ 1ኛ አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአባታቸውን ድርሻ 1/5ኛ ብር 2250.00 ለእያንዳንዳቸው 2ኛ ተጠሪ ልትከፍል ይገባል፡፡ 4ኛ አመልካችም ከሰበሰበው ብር 15,000.00 ላይ ለ1ኛ አመልካች፤ ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአባታቸውን ድርሻ 1/5ኛውን ብር 750.00 ለእያንዳንዳቸው ሊከፍል እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ እና 4ኛ አመልካች ክስ ከቀረበበት ግዜ በኋላ የድርሻቸውን እስከሚከፋፈሉ ድርስ ያለውን የኪራይ ገቢ የድርሻቸውን እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የቤ.ቁ 029 በሆነው ቤት ላይ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ በመሰረዝ ትእዛዝ ሰጥቶ፤ ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ጭብጥ በያዘባቸው ጉዳዮች ላይ የተጠሪዎችን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔዎች በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት መብት ይገባናል ብለን የተከራከርነው አመልካቾች እና ተጠሪዎች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ብቻ ነን። ምንም አይነት የመብት ጥያቄ ባልተነሳበትና የክርክርም ጭብጥ በሌለበት በተሰረዘ ኑዛዜ ለአውራሻችን የወንድም ልጅ ለወ/ሮ ሸዋረጋ ወርቁ ከህግ አግባብ ውጪ የተሰጠው የውርስ መብት ተሰርዞ ወራሾቹ አመልካቾች አባታችንን ተክተን በአንድ ዘንግና ተጠሪዎች በጠቅላላ 3 የሚቿ አውራሻችን ወራሾች ብቻ ናቸው። መብት ላልጠየቀና ግራቀኛችን ስንከራከር በአንድ ቀበሌ ውስጥ አብረው እየኖሩና ክርክሩን እያወቁ ቀርበው መብት አለኝ ላላሉ ወገኖች ባልተጠየቀ ዳኝነት የሚሰጥ ውሳኔ የለም እንዲባል።

በአማራጭ አቶ ሰለሞን አለማየሁም ሆነ ልጆቹ እነ ወይንሸት ሰለሞን በዚሁ ክ/ከተማ እና ወረዳ አመልካቾች እና ተጠሪዎች ከምንከራከርበት ሀብት ያላነሱ የመኖሪያ እና የንግድ ቤቶችን ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች ወራሾች ሆነው የውርስ ድርሻ ያገኙ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ የውርስ ድርሻ ሳይጠይቁ ሊሰጣቸው አይገባም። ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል።

የሟች አውራሻችን የውርስ ሀብቶች ይኅውም በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙት የቤት ቁጥራቸው 008፤ 008/009 እና 029 የአመልካቾች እና የተጠሪዎች የጋራ የውርስ ሀብቶች ናቸው። የስጦታ ማስረጃ ባልቀረበበት እና በተሻረ የኑዛዜ መብት መነሻነት የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በሚል የተሰጠው ውሳኔ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት ቅሬታው አያስቀርብም ሲል የሰጠው ትእዛዝ እንዲሻር እና ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ተብሎ እንዲወሰን።

የቤት ኪራይ ገቢውም በሰው እና በሰነድ ማስረጃዎች በተረጋገጠው መሰረት ከቤ.ቁ 008፤ 008/009 የሚገኘው ወርሃዊ የኪራይ ገቢ በ2ኛ ተጠሪ የሚሰበሰበው የኪራይ መጠን በወር ብር 3,500.00 መሆኑ እና ከቤ.ቁ 029 በ1ኛ ተጠሪ የሚሰበሰበው ወርሃዊ የኪራይ ገቢም ብር 16,000.00 መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ በክሱ የውርስ ድርሻ ከተጠየቀበት ግዜ እና የውርስ ሀብቱን ድርሻ አመልካቾች እስከምናገኝበት ግዜ ድረስ ያለው የገንዘብ መጠን ተሰልቶ እንዲከፈለን ውሳኔ እንዲሰጥልን የሚል ነው።

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ ለተባሉ በመዝገቡ ውስጥ ተከራካሪ ላልሆኑ ወገኖች የውርስ ሀብት ባለቤት እንዲሆኑ ያሳለፉት ውሳኔ እና የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤትም የ1ኛ ተጠሪ የግሉ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ መስፈርቱን ያሟላ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ2/5/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ተጠሪዎች በ25/5/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ጠይቀዋል።

አመልካቾች በ17/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ፤ አቤቱታው ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል።

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤ.ቁ 029 የሆነውን ቤት በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ የቤ.ቁ 029 ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በህይወት ሳሉ ለ1ኛ ተጠሪ በስጦታ ሰጥተውት በራሱ ወጪ የሰራቸው ቤቶች ስለመሆናቸው ፍሬነገርን የማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበለትን ምላሽ መርምሮ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሻሻለ እንጂ ያልተሻረ መሆኑንም ጭምር የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የቤ.ቁ 029 የሆነው ቤት የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት ነው፤ ከዚሁ ቤት 1ኛ ተጠሪ የሰበሰበው የኪራይ ገንዘብም የውርስ ሀብት አይደለም በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ የተባሉትን ሰዎች በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ የሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ወራሾች (ሌሎች ወራሾችም ያሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) መሆናቸው እና ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በ2/2/93ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሻሻለ እንጂ ያልተሻረ ስለመሆኑ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ባየው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ከሆነ ደግሞ የሟች ወራሾች የሆኑት ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁ በጉዳዩ ላይ አለመከራከራቸው ከሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ የውርስ ሀብት ድርሻቸውን እንዳያገኙ እንዲሁም አመልካቾች ከውርስ ሀብት ከሚደርሳቸው ድርሻቸው በላይ እንዲያገኙ የማያደርጋቸው በመሆኑ ከዚህ አንጻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሸዋረጋ ወርቁ እና ሰለሞን አለማየሁን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ በኮ.መ.ቁ 116047 በ21/9/12ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 257494 በ10/10/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

4. በዚህ መዝገብ በ24/6/14ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ክልል ውስጥ የሚገኙ የቤት ቁጥራቸው 008፤ 008/009፤ 029 የሆኑ ቤቶች እንዳይሸጡ፤ እንዳይለወጡ በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን ሳይተላለፉ ባሉበት ሁኔታ ተከብረው እንዲቆዩ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለየካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር እንዲሁም ለየካ ክ/ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም